November 22, 2014

# ጥሪ ለናሽቪል ደብረ ቀራኒዮ መድኃኒአለም ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስትያን ምዕመናን

ነገር ግን ሰው እንደሚገባ ቢሰራበት ሕግ መልካም እንደ ሆነ እናውቃለን።
**፩ኛ ወደ ጢሞቴዎስ፩-8**

ከሁሉ አስቀድሞ የሀያሉ የእግዚአብሄር ሥም የተመሰገነ ይሁን።

1) የዚህ ደብዳቤ ጥሪ ለማን ነው?

በአሁኑ ሰዓት ከመቼውም ጊዜ በላቀ ሁኔታ በቤተክርስቲያናችን ላይ አደጋ እየተጋረጠብን ስለሆነ ቤተክርስቲያናችንን ለማዳንና መተዳደሪያ ደንባችን ለማስከበር በደብረ ቀራንዮ መድኃኒያለም የኢኦተቤ/ክ ውስጥ ለሚገኙ አባላትና ለመሰል "ገለልተኛ" ቤተ ክርስቲያናት የቀረበ ጥሪ ነው።

2) የደብረ ቀራንዮ ቤ/ክ መተዳደሪያ ደንብ ምን ይላል?

በመተዳደሪያ ደንቡ መግቢያ ገፅ 2 ላይ "ዛሬ በአገር ውስጥም ሆነ በውጭ አገር የሚገኙ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያናት አመራር ውስጥ እየታዩ ያሉ ከፋፋይ ልዩነቶች ወደ እኛ እንዳይዛመቱና በቤተክርስቲያናችን ምዕመናን መካከል ያለው እምነትና አንድነት የጠነከረ እንዲሆን..." ከዚያም ዝቅ ብሎ ደግሞ "...እነዚህ ተጨባጭ ሁኔታዎች ተለውጠው አንድ ወጥ የሆነ የሲኖዶስ ማዕከላዊ አመራር መኖሩ እስኪረጋገጥ ድረስ ለጊዜው በየትኛውም የሲኖዶስ ማዕከላዊ አመራር ስር ራሱን ማደራጀትና ቀጥተኛ አመራር ተቀብሎ በሥራ ላይ ማዋል ያዳግተዋል።" ይላል።

3) ከዚህ በፊት ወደ ደብረ ቀራንዮ ቤ/ክ የመጡት ጳጳሳት እነማን ናቸው?

ከዚህ በፊት ወደ ደብረ ቀራንዮ ቤ/ክ የመጡት ጳጳሳት ስም ዝርዝር እንደሚከተለው ነው።

አቡነ ዮስታቲዎስ - ከአዲስ አበባው ሲኖዶስ
አቡነ ፋኑኤል - ከአዲስ አበባው ሲኖዶስ
አቡነ አብርሃም - ከአዲስ አበባው ሲኖዶስ
አቡነ ገብርሄል - ገለልተኛ ግን ወደ አዲስ አበባው ሲኖዶስ የገቡ
አቡነ ማትያስ - - ከአዲስ አበባው ሲኖዶስ (አሁን ፓትርያርክ የሆኑት)
አቡነ መልከፀዲቅ - በስደት ከሚገኘው ሲኖዶስ (የቀራንዮ ቤ/ክ መስራች አባት)

ለምን አብዛኛው ጳጳሳት ከአዲስ አበባው ሲኖዶስ ሊመጡ ቻሉ? ቤተክርስቲያናችን "ገለልተኛ" ከሆነችስ በስደት ከሚገኘው ሲኖዶስ ለምን ጳጳሳት እንዲመጡና እንዲባርኩን ጥረት አልተደረገም? ይህ ጥያቄ ቀደም ባሉትም ሆነ በአሁኑ የአስተዳደር ቦርድ አባላት በኩል ምላሽ የሚያሻው ጥያቄ ነው።

የቤተ ክርስቲያናችን መስራች አባት አቡነ መልከፀዲቅ በስደት ከሚገኘው ሲኖዶስ ስር እንድንተዳደር በአካል ጠይቀውን ነበር። በወቅቱ የነበረው የአስተዳደር ቦርድ "የመተዳደሪያ ደንባችን መመሪያ አይፈቅድም" በማለት የመተዳደሪያ ደንቡን አስከብሯል።

በሌላ በኩል ደግሞ ከአዲስ አበባው ሲኖዶስ ወገን አቡነ አብርሃም ጠንከር ያለ ደብዳቤ በመፃፍ "ቤተክርስትያኑ መቼ እንደተመሠረተና በማን እንደተመሠረተ፣ ከዚህም ጋር የቤተክርስቲያኑ መተዳደሪያ ደንብ፣ ቤተክርስቲያኑ ሲመዘገብ በማን ሥም እንደተመዘገበ፣ <u>ንብረትነቱ የማን እንደሆነ</u>፣ የደብሩ አስተዳዳሪ በማን እንደተሾሙ የሚገልፅ ማስረጃ እድትልኩልን" ይላል።

እንግዲህ ያኔ መጠለያ አጥተን በየካቶሊክ ቤተክርስቲያን ስንከራተት ዞር ብሎ ያላየን የአዲስ አበባው ሲኖዶስ - የቤተክርስቲያኗን ንብረትና የእኛን ገንዘብ እንጂ የቤተ ክርስቲያን አካል የሆንነውን <u>እኛ ኢትዮጵያውያኖችን እንደማይፈልጉን</u> አስረግጠው አሳይተውናል።

4) በአሁኑ ሰዓት ቤተክርስቲያናችን ውስጥ ምን እየተደረገ ነው?

የኢትዮጵያዊነት እና የሀገራችን የረጅም ዘመን ታሪክ ምንጭ የሆኑትን አብያተ ክርስትያናትንና ገዳማትን በማፈራረስ መነኩሳት ሲሰደዱና ሲሰቃዩ የአዲስ አበባው ሲኖዶስ አንድም ቃል ትንፍሽ ኣላለም። ምክንያቱም የአዲስ አበባው ሲኖዶስ የወያኔ መሳሪያ ነውና። ተደጋግሞ እንደታየው ወያኔ እጁን ወደ ውጪ አገራት በሚገኙት "ገለልተኛ" ቤ/ክ ላይ አዋጅ አውጆ ወደ አዲስ አበባው ሲኖዶስ እንዲቀላቀሉ ካልሆነ ግን በቤ/ክ ውስጥ ሰላም እንዳይሰፍን ለማድረግ ደጋፊዎቹን

በአባ ፋኑኤል (የዋሽንግተን ዲሲ ጳጳስ) በኩል አሰማርቷል። ስለሆነም በተጨባጭ እንደምናየው የወያኔ አስተዳደር በተግባር ደጋፊዎቹን አሰማርቶ በቤተክርስቲያናችን ውስጥ ሰላም እንዳይሰፍን እያደረገ ይገኛል። የቤተክርስቲያኗን ንብረት ለመውሰድም አሰፍስፎ ይገኛል። ልብ ማለት ያለብን ገንዘባችንና ንብረታችን እንጂ እኛ ኢትዮጵያውያኖች በወያኔና በአዲስ አባባው ሲኖዶስ ዘንድ አንፈለግም።

5) በቤተ ክርስቲያናችን ውስጥ ለዚህ ጉዳይ የተመደቡና የሚከፋፍሉን እነማን ናቸው?

በአሁኑ ወቅት እውነተኛ የኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን “አማኝ” መስለው ነገር ግን በወያኔ መዋቅር ውስጥ ሲያገለግሉ የነበሩና እያገለገሉ ያሉ ታጋዮች (ወታደሮችና ፖሊሶች)፤ ካድሬዎች በቤተ ክርስቲያናችን ውስጥ ተሰግስገው ይገኛሉ። እየከፋፈሉንና እያመሱን የሚገኙት የወያኔ አባላቶች ናቸው። በናሽቪል ደብረ ቀራኒዮ መድኅኒአለም ቤተክርስቲያን ንብረት ላይ የይገባኛል ጥያቄ ሲነሳ ይህ የመጀመሪያ ጊዜ አይደለም ይህ የመጨረሻውም አይሆንም።

6) ምን እናድርግ?

ሀ) ህወሃት በአሜሪካ መንግስት ዘንድ “ሽብርተኛ” ነው ከተባለ ከ30 ዓመታት በላይ አስቆጥሯል[1]። ለዚህ መረጃ ከግርጌ ይመልከቱ። ስለዚህ በአገር ቤት ውስጥ ወንጀል ሰርተው በመካከላችን የተደበቁትን የሚጋለጡበትን ሁኔታ ማመቻቸትና ለህግ አጋልጦ ማቅረብ።

ለ) መተዳደሪያ ደንባችን እንዲከበር ማድረግ።

ሐ) የሲኖዶስ አባል መሆን የፈለጉ ግለሰቦች - በከተማችን ውስጥ በሁለቱም ሲኖዶሶች የሚተዳደሩ አድባራት ስለሚገኙ ወደዚያ እንዲሄዱ መንገዱን ማሳየት።

መ) የወቅቱ ጥያቄ ተቀባይነት ካጣውና እየወደቀ ካለው የወያኔ የኃይማኖት ክፍፍል ሴራ ጋር ምንም ዓይነት ግንኙነት አለመፍጠር፤ በታሪክም ተወቃሽ ላለመሆን የተንኮል ሴራውን ማክሸፍ እንድንችል ጥሪ እናደርጋለን።

ወስብሀት ለእግዚአብሄር

**በቴኒሲ ናሽቪል የቀራኒዮ መድኅኒአለም ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስትያን ገለልተኝነት ጠባቂ ግብረ ኃይል**

---

[1] **ምንጭ፡** http://www.start.umd.edu/gtd/search/Results.aspx?search=Tigray+Peoples+Liberation+Front+&sa.x=38&sa.y=14

The Tigrayan People's Liberation Front (TPLF) is a political party in Tigray, Ethiopia that has been listed as a perpetrator in the Global Terrorism Database, based on ten incidents occurring between 1976 and 1990

| GTD ID | DATE | COUNTRY | CITY | PERPETRATOR | FATALITIES | INJURED | TARGET TYPE |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 199008020002 | 1990-08-02 | Ethiopia | Ray Kobo Province | Tigray Peoples Liberation Front (TPLF) | 17 | 0 | Religious Figures/Institutions |
| 198802180001 | 1988-02-18 | Ethiopia | Tigre Province | Tigray Peoples Liberation Front (TPLF) | 0 | 0 | Private Citizens & Property,NGO |
| 198410190003 | 1984-10-19 | Ethiopia | Lalibela | Tigray Peoples Liberation Front (TPLF) | 200 | 200 | Private Citizens & Property |
| 198308030001 | 1983-08-03 | Ethiopia | Jari | Tigray Peoples Liberation Front (TPLF) | 0 | 0 | NGO |
| 198304200006 | 1983-04-20 | Ethiopia | Korem | Tigray Peoples Liberation Front (TPLF) | Unknown | Unknown | NGO,NGO,NGO |
| 197905020020 | 1979-05-02 | Ethiopia | Workamba village* | Tigray Peoples Liberation Front (TPLF) | 100 | 0 | Private Citizens & Property |
| 197905020019 | 1979-05-02 | Ethiopia | Aksum | Tigray Peoples Liberation Front (TPLF) | Unknown | Unknown | Private Citizens & Property |
| 197811000005 | 1978-11-00 | Ethiopia | Unknown | Tigray Peoples Liberation Front (TPLF) | 0 | 0 | Business |
| 197607250001 | 1976-07-25 | Ethiopia | Unknown | Tigray Peoples Liberation Front (TPLF) | 0 | 0 | Journalists & Media |
| 197605000003 | 1976-05-00 | Ethiopia | Tigre Province | Tigray Peoples Liberation Front (TPLF) | 0 | 0 | Private Citizens & Property |

**ምንጭ፡** http://www.start.umd.edu/gtd/search/Results.aspx?search=Tigray+Peoples+Liberation+Front+&sa.x=38&sa.y=14